# የፍልስጥኤማውያን እንባ

መስፍን ወልደ ማርያም

ጥር 2001

በአለፉት ሳምንታት በፍልስጥኤማውያን ላይ ከሰማይ የሚዘንብባቸው እሳት፣ ከመሬት የሚወነጨፍባቸው የታንክ፤ የመድፍና የመትረየስ ጥይትና ቦምብ ሊመክቱትና ሊቋቋሙት የማይችሉት ነበር፤ አንድ በዘመናዊ የሳይንስ ጥበብ የሠለጠነ አገር፣ በአሜሪካ ሀብትና ኃይል እየታገዘ በምስኪኖቹ የጋዛ ፍልስጥኤማውያን ላይ በየዕለቱ የሚፈጽመው ግፍ በ1928 በፋሺስት ኢጣልያ በኢትዮጵያ ላይ የተፈጸመውን በግድ ያስታውሳል። ያኔም ዓለም ዝም ብሎ ተመለከተ፤ ዛሬም ዝም ብሎ ይመለከታል።

በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ዘመናት ይሁዲዎች አስከፊ ግፍን በጸጥታ ሲቀበሉ ነበር፤ በዚያን ጊዜ አገር አልነበራቸውም። ሁለተኛው የዓለም ጦርነት እንዳበቃ በሽብር የእንግሊዞችን አገዛዝ ሽረው፣ አረቦቹን ከመኖሪያቸው አፈናቅለው ከተለያዩ የምዕራብ አገሮች ተሰባስበው እሥራኤል የሚባል አገር በፍልስጥኤማውያን አገር ላይ ፈጠሩ። ከዚያ በኋላ የአገሩ ባለቤቶች የነበሩት ፍልስጥኤማውያን በገዛ አገራቸውም፣ በሌሎች አገሮችም ስደተኞች ሆኑ፤ አገር ያልነበራቸው ይሁዲዎች የአገሩ ባለቤት ሆነው ራሳቸውን ተከሉ።

የዛሬ ሃምሳ ዓመት ግድም ይሁዲዎቹ አረቦቹን ከአገራቸው ሲያስወጡ በነበሩበት ጊዜ በዓለም የታወቀው እንግሊዙ የታሪክ ፈላስፋ አርኖልድ ቶይንቢ በሞንትሪአል ዩኒቨርሲቲ ንግግር ሲያደርግ አዲስ ሀሳብ አቅርቦ ነበር፤ በቶይንቢ አስተሳሰብ አንድ ግፍን ሲቀበል የኖረ ሕዝብ ጊዜ ሲያጋጥመውና ጉልበት ሲያገኝ በሱ ላይ የተፈጸመበትን ግፍ በሌሎች ላይ ይፈጽማል፤ ለዚህም ይሁዲዎች በአረቦች ላይ እየፈጸሙ ያሉት ግፍ ማስረጃ ይሆናል ብሎ ነበር፤ ከያለበት ቢንጫጩበትም አስተሳሰቡን ሊለውጡት አልቻሉም። ቶይንቢ በሕይወት ቢኖር ዛሬ በጋዛ የሚደረገው የማንአለብኝነት ጭፍጨፋ አስተሳሰቡን የሚያረጋግጥለት መሆኑን ይረዳ ነበር።

ይሁዲዎች የደረሰባቸውን ግፍ በጭራሽ ለመርሳት አይፈልጉም፤ በነሱ ላይ ግፍ የፈጸመውን ሁሉ ከካናዳ እስከአውስትራልያ እያደኑ ለፍርድ ያቀርቡታል፤ በይሁዲዎች ላይ የደረሰውን ግፍ ትንንሾች ልጆች ሁሉ እንዲያውቁት በስዕል የተደገፈ ትምህርት ይሰጣቸዋል፤ በየቦታው መዘክረ ግፍ አቋቁመዋል፤ የደረሰባቸውን ግፍ ሊረሱት አይፈልጉም፤ በነሱ ላይ ግፍ ለፈጸሙባቸው ሰዎች የምሕረት ልብ የላቸውም፤ ዛሬ እነሱ ግፍ ለሚፈጽሙባቸውም ሰዎች ምሕረት የላቸውም።

ፍልስጥኤማውያን መሬታቸውን ተቀምተው፣ ዙሪያቸውን ታጥረው፣ መውጫ መግቢያቸው በእሥራኤል ቁጥጥር ስር ሆኖ፣ ፍልስጥኤማውያን በድንጋይ እሥራኤላውያን በታንክና በአውሮጵላን ሲደባደቡ ብዙ ዓመታት አለፉ፤ በአሜሪካ ቁጥጥር ስር ያለው የተባበሩት መንግሥታት ውሳኔዎችን ከማስተላለፍ በቀር ምንም ፋይዳ ያለው መፍትሔ ሊያስገኝ አልቻለም። የአረብ አገሮች ቀደም ሲል ከፍልስጥኤማውያን ጋር ባሳዩት ትብብር ከእሥራኤል ጋር በጦርነት ተዋግተው የእሥራኤልን ጡንቻ ቀምሰው ስለነበረ ተኮማትረው ወደገለልተኛ መሳይ አስታራቂነት ገብተዋል፤ ስለዚህም ዛሬ የጋዛ ፍልስጥኤማውያን የእሥራኤልን ከፍተኛና ዘመናዊ ኃይል የገጠሙት ብቻቸውን ነው። የእሥራኤል ማንአለብኝነት ሀኪም ቤቶችን፣ ትምህርት ቤቶችን፣ መኖሪያ ቤቶችንም ሳይለይ፣ ከዚያም በላይ በቀይ መስቀል፣ በተባበሩት መንግሥታት ትምህርት ቤት፣ በተባበሩት መንግሥታት የእርዳታ ድርጅት

ላይም ሳይቀር የማንደድና የማውደም ኃይሉን አሳይቷል። በአጭር ጊዜ ውስጥ ከአንድ ሺህ ሁለት መቶ በላይ ፍልስጥኤማውያን ተገድለዋል፤ ከነዚህም ውስጥ ሢሶ ያህሉ ሕፃናት ናቸው ይባላል፤ የተጎዱት ሰዎች ቁጥር ከአምስት ሺህ በላይ ነው ይባላል። በንብረት ላይ የደረሰው ጥፋት በጣም ከባድ ነው።

ከሃምሳ ዓመታት በፊት የደረሰበትን ግፍ መርሳት ያቃተው ሕዝብ ለሚቀጥሉት ሃምሳ ዓመታት ቂምን የሚያስረግዝ ግፍ የሚፈጽምበት ምክንያት ምን ይሆን? ለምንስ ይጠቅማል? አንድ ሕዝብን መጨረስ እንደማይቻል ይሁዲዎች በራሳቸው የቅርብም የሩቅም ታሪክ አይተውታል፤ የዓለም ሁኔታም ለዘለዓለም ረግቶ እንደማይቆይ ከነሱ የበለጠ የሚያውቅ የለም፤ የዱሮው የደቡብ አፍሪካ ፕሬዚደንት ደ ክለርክ በቅርቡ ከአንድ ቴሌቪዥን ጋር በተደረገ ቃለ ምልልስ የዱሮውን የደቡብ አፍሪካ የባንቱስታን ክልሎች አገዛዝ ከእሥራኤልና ከፍልስጥኤም ጋር አወዳድሮ በመሬት እየተጣሉና እየተጋጩ መኖር አይቻልም፤ የሚጠቅመው አብሮ በዴሞክራሲ ሥርዓት ስር መኖር ነው በማለት ሁሳቡን ገልጾ ነበር፤ ይህ ለይሁዲዎቹ የሚዋጥላቸው አይደለም።

በእሥራኤል በኩል በጣም ጎልቶ በተደጋጋሚ የሚነገረው ሮሮ ፍልስጥኤማውያኑ ወደእሥራኤል የሚወነጭፉት ፈንጂ ነው፤ ስንት መቶ ተወንጫፊ ተወርውሮ በእሥራኤል ላይ በሕይወትም ይሁን በንብረት ላይ ያደረሰው ጥፋት በአሁኑ በፍልስጥኤም ጦርነት ጊዜ የእስራኤል ወታደሮች ከገደሏቸው የራሳቸው ሰዎች ቁጥር አይበልጥም፤ ለነገሩ ፍልስጥኤማውጣን ወደእስራኤል የሚወነጭፉት መጫወቻ አይሉት፣ የጦር መሣሪያ አይሉት ነገር ለመተንኮስ እንጂ ለመጉዳት የታቀደ አይመስልም፤ ተንኩሶ የበለጠ ጉዳትን መጋበዝ የሚያስፈልገው ለምን እንደሆነ ግልጽ አይደለም፤ ፍልስጥኤማውያን እሥራኤል በመረጠላቸው የትግል ዘዴ ለነጻነታቸው መታገሉ የሚበጃቸው አይመስልም። የሰሞኑ ጭፍጨፋ ለፍልስጥኤማውያን አንድ ነገር ሊያስተምራቸው ይገባል፤ ልክ የሌሎች ሕይወትና የምዕራባውያን ሕይወት በእኩል እንደማይመዘነው፣ የይሁዲዎች ሕይወትና የፍልስጥኤማውያን ሕይወት እኩል አይመዘንም፤ ለእሥራኤል የአንድ ይሁዲ ሕይወት ትልቅ ጉዳት ነው፤ በአንጻሩ የፍልስጥኤማውያን ሕይወት ምንም ያህል ዋጋ የለውም። ሌላ ቢቀር የፍልስጥኤማውያን የነጻነት ትግል ለፍልስጥኤማውያን ሕይወት ከፍ ያለ ግምት ይዞ መቀጠል አለበት። የእሥራኤልን ጉልበት ማዳከም የሚቻለው ድንጋይ በመወርወር ሳይሆን የሚፈጽሙትን ግፍና ጭካኔያቸውን በማጋለጥ ነው።